# <u>*ምንም ሳለመተካት:መተካካት*</u>

*አሥራደው (ከፈረንሳይ)*

*ሰሞኑን የአቶ መለስ ዜናዊ መታመም ጉዳይ: በአገር ውስጥና፤ ከአገር ውጪ ባሉት የሥርአቱ ደጋፊዎች ዘንድ፤ እንዲሁም የአቶ መለስ የጡት አባቶች በሁኑት ምዕራባዊ አገራት፤ በአፍሪካ የዕድሜ ልክ ሥልጣን ባለቤቶች፤ የኢትዮጵያ መሬት በርካሽ በተቸበቸበላቸው የአረብ አገራትና፤ በተጨማሪም የአገራችን በር ወለል ተደርጎ ተከፍቶላቸው እንደልባቸው በሚምነሸነሹት ቻይናና ሕንዶች ሳይቀር፤ የስጋት አውሎ ንፋስ አንፍሿል ::*
*ስሜቱ እንደሰው መልክና ጠባይ፤ አመለካከትና ስሌት፤ አስተዋይነትና ቸልተኝነት፤ የአይምሮ ምጥቀትና ጥበት፤ የኑሮ ምቾትና ስቃይ፤ ሃይማኖትና ዕምነት፤ አብሮ አደግና ጓደኝነት፤ ቀለምና ዝርያ፤ ጥቅምና ጉዳት፤ ፖለቲካዊ ሽፍጥና ተአማኒነት፤ ዝርፊያና ታማኝነት፤ ጎሳና ነገድ፤ አብሮነትና መነጣጠል ...........ወዘተ ዝንጉርጉር ነው ::*

*በሥርአቱ ደጋፊዎች ዘንድ፤ ስጋት፤ ጥርጣሬ፤ ፍራቻና ድንጋጤ እየቀላቀለ፤ ውሉ ያለየለት ትኩሳት እየፈጃቸው፤ ቁልቁል ሲያስምጣቸው፤ ሽቅብ ሽቅብ ሲላቸው፤ አካላቸው ሲርድ፤ እግራቸው ሲብረከረክ፤ አልፎ አልፎም ሆዳቸውን ባር ባር እያለው በዝምታ ባሕር ተውጠው፤ የዘረፉትን የአገር ሃብት በየትኛው ቀዳዳ እንደሚጨምሩ፤ በየትኛው ጉርጓድ እንደሚቀብሩ፤ ወይም ወደ የትኛው አገር፤ በማን ስም እንደሚያሸሹት፤ በየት በኩል ከአገር ሹልክ ብለው እንደሚያመልጡ ሌት ተቀን በማሰላሰል፤ ድብልቅልቅ ባለ ውሉ በጠፋበትና፤ ባልታወቀ ስሜት ውስጥ ሆነው ይወራጫሉ፤*

*በአገር ውስጥና ከአገር ውጪ ያሉ የሥርአቱ ተቃዋሚዎች ደግሞ፤ የተለያዩ መላምቶችን ይወነጫጭፋሉ፤................*

*በአገር ውስጥ የሚገኙና ሥርአቱን የሚቃወሙ ዕድሜ ጠገብት ምሑራን ፍራቻቸውን ገልጠው ኢትዮጵያ እንደማትፈርስ ከገለጹ በኋላ፤..................... መፍትሄውን፤ በጸሎት ሲደመድሙ፤*

*አንዳንዶቹ ደግሞ አቶ መለስ ዜናዊ በአጋዚ ሠራዊታቸው ያስፈጇቸው እነ ሸብሬና አብረዋት መሰዋዕት የሆኑት ወገኖቻትን ሕይወት ሳይሆን፤ የአቶ መለስ ዜናዊ ጤንነት ይበልጥ አስጨንቋቸው፤ የስልጣን ክፍተት እንዳይፈጠር የወያኔ (ኢህአዴግ) ባለስልጣናት የአቶ መለስን ጤንነት እንዲነግሯቸው ከመማጠናቸው በላይ፤ የሰው ልጆችን ግፍና፤ በደል ወደማያይ፤ የሳቸው ብቻ ወደሆነው አምላክ፤ እንደሚጸልዩ ተናግረዋል ::*

*በኢትዮጵያ ሕዝብና፤ በራሳቸው የፖለቲካ ድርጅት አባላት ጭምር ሳይቀር አፈና፤ እንግልት፤ የዕድሜ ልክ እስራት፤ ግድያና በጥቅሉ የሰብአዊ መብት ገፈፋ የሚፈጽም አምባ ገነን መንግሥት፤ በስብሶ ለመውደቅ በሚንገዳገድበት ወቅት ገፍቶ በመጣል ፋንታ ሰለለሱ ጤንነት መጨነቅና መጸለይ አሳፋሪ ነው ::*

ያለውን ጨቋኝና አፋኝ ሥርአት እታገላለሁ ከሚል የፖለቲካ ድርጅት፤ አመራር የምንጠብቀው፤ ከጉንጭ አልፋ ዲስኩርና፤ ከሬራ ተባ የወረቀት ላይ መግለጫ ባሻገር፤ ሕዝቡን አስተባብሮ በማደራጀት፤ በማሰባሰብ፤ ሰላማዊ ሰልፍ በማድረግ፤ የሥራ ማቆም አድማ በመጥራት፤ ወሳኝ የሥርአት ለውጥ እንዲደረግና፤ ለሕዝብ ፈቃድ ተገዢ የሆነ ስርአት እንዲመሰረት መጣር መሆን ሲገባው፤ ለአንባ ገነን ስርአት የአዞ እንባ ማንባት መሆን የለበትም ::

ወያኔ እራሱ ያወጣውን ሕግ እየጣሰ፤ የህግ የመላይነት ጠፍቶ አገር እየታመሰ፤ ሠላም ሳይኖር፤ ሠላማዊ ትግል እያሉ ሕዝቡን ማዘናጋት፤ « ላም ባልዋለበት ኩበት ለቀማ » ከመሆኑም በላይ ሕዝብ ለመብቱ ቆርጦ እንዳይታገል ትጥቅ እንደማስፈታት ይቆጠራል ::

አፋኙ የወያኔ አገዛዝ በፈጠረው ባዶነት (vacuum) በአሁኑ ጊዜ እየገነፈለ ያለውን የሕዝብ ብሶት በትክክለኛው ቦይ እንዲፈስ በማድረግ ዘረኛውን አስተዳደር ጠራርጎ በማስወገድ፤ ፍትህ፤ ዕኩልነት፤ ሠላምና ብልጽግና በመላው ኢትዮጵያ እንዲሰፍን ለማድረግ የተዘጋጀ ጠንካራ የፖለቲካ ድርጅት ባይኖርም፤ ፍላጎቱ ካለ አሁንም ይቻላል ::

አሁንም አፋኙ የወያኔ አገዛዝ በፈጠረው የመሪነት ባዶነት (Leadership vacuum) በሕዝብ ዘንድ ተቀባይነት ያለው፤ የሕዝቡን የልብ ትርታ ሊያዳምጥ የሚችል፤ በሕዝብ መሃል ሆኖ የህዝቡን ሙቀት የመለካት ብቃት ያለው፤ የማዳመጥ ችሎታው የዳበረ፤ ትዕግሥትን የተላበሰ፤ የመናገር ክህሎት ያለው፤ ቆራጥነትና አስተዋይነት የተካነ፤ ከምንም በላይ ለአገራችን ደህንነትና ለህዝቦቿ ጥቅም የሚጥር፤ ለጋራ እሴቶቻችን ጥብቅና የቆመ፤ ከልዩነታችን ይልቅ ለአብሮነታችን አጽንኦት የሚሰጥ፤ አስተዋይ መሪ የመኖሩ ወይም የማግኘቱ ጉዳይ ዋናው ሲሆን፤ ፍጹም የለም ማለት ግን አይቻልም ::
ኢትዮጵያ ብዙ የተማሩ አስተዋይና ለአገራቸው ከፍታኛ ፍቅር ያላቸው ዜጎች ስላሏት ፍላጎቱና ቆራጥነቱ ካለ አሁንም ይቻላል::

በአንጻሩ የወያኔ (ኢህአዴግ) ከፍተኛ ባለስልጣናት የመረጡት ዝምታን፤ አልፎ አልፎ ማስተባበያን፤ አለያም በመንግሥት ቃል አቀባዩ አቶ ሰብሃት ነጋ በኩል « መለስ ኖረ አልኖረ ስርአቱ አይነቃነቅም » መለስ ቢሞት እኛ እንተካለ የሚል ድንፋታ መሰል መግለጫ ሲሆን፤ እኛ ደግሞ « **ጉልቻ ቢቀያየር ወጥ አያጣፍጥም** » የሚለውን የቀድሞ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄን ብሂል እናስታውሳቸዋለን ::
አቶ መለስ ድነው ተመለሱም አልተመለሱ፤ ከአሁን በኋላ የአቶ መለስ ዜናዊ ጉዳይ « ሽክላ ከነቃ አይሆንም ዕቃ » ነውና፤ የወያኔ (ኢህአዴግ) አባላት ስለ አቶ መለስ ዜናዊ ጤንነት ተናገሩ አልተናገሩ፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ ለሥርአቱ ያለውን ጥላቻና፤ ለለውጥ ያለውን ፍላጎት ሊያዳፍነው አይችልም ::
ኢትዮጵያ በሕመምተኛ ፕሬዚዳንትና በሕመምተኛ ጠቅላይ ሚንስተር እየተመራች፤ የታመመች አገር ከሆነች ይኸው ድፍን 21 ዓመታት አስቆጠረች ::
ታዲያ ለ21 ዓመታት ከጠሏት፤ ካደሟት፤ ካሳመሟት፤ እየዘረፉ ካዘረፏት፤ ዜጎቿን በጎሳ፤ በዘርና በሃይማኖት ከፋፍለው ከሚያምሷት አቶ መለስ ዜናዊ ኢትዮጵያ ብትገላገል ስጋቱና ፍራቻው ምንድነው ?!

*እንኳን አቶ መለስ ዜናዊ፤ ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለስላሴ፤ ሰዩመ እግዚአብሔር እየተባሉ፤ እሳቸው ከሞቱ ኢትዮጵያ ሰማዩ የሚደፋባት፤ መሬቱ የሚገለበጥባት፤ አገር ትሆናለች የተባሉትም ሞተዋል ! ኤላስ !! ኢትዮጵያ ግን፤ ብትታመምም አሁንም አለች !!*

*መለስ ዜናዊ ከሌሉ ኢትዮጵያ ትበታተናለች፤ እያሉ የሚያስወሩ መለስን እንደ ጣኦት ለሚያመልኩ የአይምሮ ስንኩላን የምንላቸው ቢኖር፤ ኢትዮጵያ እንድትበታተን ሌት ተቀን ተግቶ የሠራው ማን ሆነና ?! አልሆን አላቸው እንጂ ! አቶ መለስና የቅርብ ጓደኞቻቸው አይደሉም ?!*
*የኢትዮጵያ ሕዝብ አርቆ አስተዋይ፤ ብልህና ታጋሽ በመሆኑ ተንኮላቸውን ተረድቶ እምቢ በማለቱ ተንኮላቸው ሳይሳካ ቀረ እንጂ፤ አቶ መለስማ ኢትዮጵያን ለመበታተን ያልፈንቀሉት ድንጋይ ያልቆፈሩት ጉርጓድ አልነበረም ::*

*በአገር ውስጥ የሚገኙና፤ ሥርአቱን ከሚቃወሙ ዕድሜ ጠገብ ምሁራን አንዱ ፍራቻቸውን ገልጠው ኢትዮጵያ እንደማትፈርስ ሲናገሩ፤*

*« ኢትዮጵያ እንድትፈራርስ የሚመኙ ጭንጋፍ ልጆችም አሏት፤ ማህጸንዋ እየደማ እየረገመቻቸው ሰላምና እንቅልፍ አጥተው አብጠው ይፈነዳሉ ! .................... አንዳንዶች ቢጨነግፉም፤ አንዳንዶች ቢክዱም፤ አንዳንዶች ሆዳም ቢሆኑም፤ አንዳንዶች ቢወላውሉም፤ ኢትዮጵያ አሁንም የሚሞቱላት ልጆች አሏት፤ ኢትዮጵያ አትፈርስም ! .................... ያልበሏት፤ የሚሳሱላት፤ ያልሸጧት፤ አፈሯን የሙጥኝ ብለው አፈርሽ እንሁን የሚሏት፤ ድህነትም ሆነ ጭቀና ካንቺ አይለየንም፤ የሚሏት ልጆች ኢትዮጵያ ዛሬም አሏት፤ አፍራሾች ቀድመው ይፈርሳሉ ! ኢትዮዮጵያ ዛሬም ልጆች አሏት ስትፈርስ ቆመው የማያዩ ! ..................................*
*ኢትዮጵያ አትፈርስም ! አፍራሾች ቀድመው ይፈርሳሉ !......................... ».*
*(ሙሉውን የፕሮፌሰር መስፈን ወልደማርያም ጽሁፍ በማጣቀሻው ያገኙታል)*
*http://ethiopiazare.files.wordpress.com/2012/07/195.pdf*

*ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት ይቀጥላል! መቀጠልም አለበት፤ ለ21 ዓመታት ታፍኖ የቆየው የኢትዮጵያውያን ልብ፤ የኢትዮጵያዊነትን ደም እንደገና መልሶ መርጨቱን ይጀምራል፤ ተቋጥረው የነበሩ የደም ስሮቻቸው ኢትዮጵያዊነትን በመላው ዜጎች ሰውነት ውስጥ ተመልሶ እየተርመሰመሰ እንዲፈስ ቦዩን ወለል አርገው ይከፍታሉ፤ በዚህም ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት እንደገና እንደ አባይ ወንዝ ጎርፉ ሞልቶ ይፈሳል ! መሬቷም ለምልሞ ይፈካል፤ አብቦ ፍሬ ያፈራልይ ! የጠላትም ቀሽቱ ያራል፤ ይበግናል! ከአሁን በኋላ* ***ምንም ሳለመተካት:መተካካት በቃ! ከመለስ ዜናዊ:ወደ መለስ ዜናዊ*** *አንመለስም !! ቆርጣችሁ ተነሱ የኢትዮጵያ ወጣቶች! እልል በሉ የኢትዮጵያ እናቶች ! ታዲያ ይህ እንዳይሆን ፍራቻው ምንድነው ?!*

*ሐምሌ 14 2004 ዓ.ም. (July 22/2012)*